Home Office

# ለጤና እና ማኅበራዊ እንክብካቤ ባለሙያዎች እንዲሁም መምህራን የሴት ልጅ ብልት ግርዛትን [female genital mutilation (FGM)] ለፖሊስ የማሳወቅ ግዴታ

## ግዴታው ምንድን ነው?

በኦክቶበር 31፣ 2015 የጤና እና የማኅበራዊ እንክብካቤ ባለሙያዎች እንዲሁም መምህራን ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች በሆኑ ልጃገረዶች ላይ በግልጽ "የታወቀ" የFGM ጥቃት በሚፈጸምበት ጊዜ ለፖሊስ እንዲያሳውቁ የሚያስገድድ ግዴታ ተጥሎባቸዋል።

ለምሳሌ አንድ ሐኪም ዕድሜዋ ከ18 ዓመት በታች የሆነች ልጃገረድ FGM መኖሩን ሲመለከት ለፖሊስ ይህንኑ የማሳወቅ ኃላፊነት አለበት። ወይም አንዲት ልጃገረድ ለመምህሯ FGM ተፈጽሞባት እንደነበረ ከነገረች መምህሯ ይህንኑ ለፖሊስ ማስታወቅ ይኖርባቸዋል።

## ጉዳዩን ፖሊስ እንዲያውቀው ከተደረገ በኋላ ምን ይፈጠራል?

FGM በጣም ከባድ ወንጀል ነው እና እያንዳንዱን ሪፖርት የተደረገ ጉዳይ ፖሊስ በአግባቡ መመርመር ይኖርበታል።

ፖሊስ ልጃገረዷ ደኅንነቷ መጠበቁን እና የእርስዎ ፍላጎቶች ከምንም በላይ ቅድሚያ እንደተሰጣቸው ለማረጋገጥ ከማኅበራዊ እንክብካቤ ባለሙያዎች ጋር አብሮ ይሠራል።

## ይህ ግዴታ ለምን ተግባራዊ ይደረጋል?

አንዲት ልጃገረድ FGM ከተፈጸመባት ወይም ተፈጽሞባት ከነበረ ከባድ ወንጀል እንደተፈጸመ ተቆጥሮ በተቻለ ፍጥነት ፖሊስ ጉዳዩ ውስጥ እጁን ማስገባቱ በጣም አስፈላጊ ነው። ይህ አሠራር አግባብነት ያለው ምርመራ ስለ መከናወኑ ማረጋገጫን ይሰጣል።

የዚህ ግዴታ ተግባራዊ መሆን ዓላማው ባለሙያ ሠራተኞች FGM ን ፊት ለፊት ለመጋፈጥ እንዲችሉ በራስ የመተማመን መንፈስ እንዲኖራቸው ለማረጋገጥ እና እያንዳንዱ ጉዳይ በአግባቡ በፖሊስ ተይዞ እንዲመረመር እንዲደረግ ወደ ፖሊስ ሪፖርት የሚደረጉ ጉዳዮችን ብዛት ለመጨመር እንዲቻል ለማገዝ ነው።

## የተቀመጠው ግዴታ የማይመለከታቸው ነገሮች

ይህ ማለት ፖሊስ ከማኅበራዊ እንክብካቤ ባለሙያዎች እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ባለሙያዎች ጋር ሳይማከር እርምጃ ይወስዳል **ማለት አይደለም**።

FGM ስለመፈጸሙ *በሚጠራጠሩበት ጊዜ* ወይም አንዲት ልጃገረድ *ጥቃቱ ሊፈጸምባት በሚያስችል አደጋ ውስጥ ሆና ስትገኝ* ለፖሊስ ጉዳዮን ሪፖርት ለማድረግ የግድ ባለሙያ **መሆን አያስፈግም**። ግዴታው ዕድሜያቸው 18 ወይም ከዛ በላይ በሆኑ ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም። በነዚህ ሁኔታዎች ላይ ባለሙያዎች ቀደም ሲሉ የነበሩ የጥበቃ ማድረጊያ የአሠራር ሂደቶችን ይከተላሉ።

### አጭር ማጠቃለያ፦ ግዴታ የሆነ የ FGM ሪፖርት አደራረግ*

ግዴታው ቁጥጥር በሚደረግባቸው በእንግሊዝ እና በዌልስ አገሮች ውስጥ በሚገኙ የጤና እና የማኅበራዊ እንክብካቤ ባለሙያዎች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

እነዚህ ባለሙያዎች በሙያዊ የሥራ ግዴታቸው ላይ እያሉ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ለፖሊስ ሪፖርት እንዲያደርጉ ይገደዳሉ፦

- ዕድሜዋ ከ18 ዓመት በታች በሆነች ልጃገረድ በላይዋ ላይ FGM ድርጊት መፈጸሙን ሲነገራቸው፤ ወይም
- ዕድሜዋ ከ18 ዓመት በታች በሆነች ልጃገረድ ላይ የ FGM ድርጊት ስለመፈጸሙ ፍንጭ ሰጪ አካላዊ ምልክቶች መኖራቸውን ሲያስተውሉ እና ይህ ድርጊት ለልጃገረዲቱ አካላዊ ወይም የአእምሮ ጤና ወይም ከምጥ ወይም ከወሊድ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ምንም አስፈላጊነት እንደሌለው ሲያምኑ።

*በክፍል 5B የ FGM  ሕግ 2003 ላይ የተደነገገ፣ በክፍል 74 ከባድ ወንጀሎች መቅጫ ሕግ ላይ በተካተተው መሠረት